# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

አቅራቢዎች



# የጌዲዮን ታናሹ ሰራዊት

ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Janie Forest, Alastair Paterson

ያሻሻለው (አሻሽሎ የጻፈው): Ruth Klassen

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጇ: Bible for Children
www.M1914.org

©2022 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።


ኢያሱ ከሞተ በኋላ ፣
የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ
በእግዚአብሔር ላይ አመጹ
እና እግዚአብሔርን
ከሕይወታቸው ውስጥ
አወጡት:: እግዚአብሔርም
በጎረቤቶቻቸው
በሚዲያማዊያን እጅ
የእስራኤል ሰብልና
ቤት እንዲቃጠል አደረገ::
እስራኤላዊያንም በዋሻ
ውስጥ መኖር ነበረባቸው::



አንድ ጌዲዮን የሚባል እስራኤላዊ ስንዴን ለማሳደግ አንድ የሚስጥር ስፍራ ያስፈልገው ነበረ፡፡ በትልቅ ዛፍ ስር ሆኖ ተደብቆ በተቀመጠ የወይን መጥመቂያ ስንዴ ይወቃ ነበረ፡፡ ምድያማዊያን ስፍራውን አያውቁትም ነበረ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ያውቀዋል፡፡ እግዚአብሔር መልአኩን ወደ ጌዲዮን መልእክት እንዲያደርስ ላከው፡፡

እግዚአብሔር በጌዲዮን አባት ምስል የተሰራውን የሐሰት አምላክ መሰዊያ እንዲያፈርስና በእግዚአብሔር መሰዊያ እንዲተካው ለጌዲዮን ተናገረው፡፡ ምንም እንኳን ጌዲዮን የሃገሩ ሰዎች ይገሉኝ ይሆናል የሚል ፍርሃት ቢኖርበትም ፣ እግዚአብሔር ያዘዘውን ነገር አደረገ፡፡



አግዚአብሔርም ጌዲዮን እስራኤላዊያንን እንዲመራና ክፉ የሆኑትን ምድያማዊያን እንዲገጥም ፈለገ። ነገር ግን ፣ ጌዲዮን ፈርቷል። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንዳለ የሚያሳየውን ልዩ ምልክት ለማየት ጠየቀ። ከዚያም ፣ በመሬቱ ላይ የበግ ቆዳን የሚመስል ነገር ጣለ።





“እርጥበት የሚመስል ነገር በቆዳው ላይ ከታየና ሌላው መሬት ሁሉ ግን ደረቅ ከሆነ” ጌዲዮንም ጸለየ “አንተው እንደተናገርከው ፣ በእኔ እጅ እንደምትታደጋቸው አውቃለሁ”።

በጠዋትም ፣ መሬቱ ደረቅ ነበረ ፤ ቆዳው ግን እጅግ ረጥቦ ነበረ።

ጌዲዮን እስካሁን በጥርጥር ውስጥ ነው፡፡ አሁን ደግሞ እግዚአብሔር ቆዳውን ሲያስቀር ሌላውን ስፍራ ሁሉ እርጥብ እንዲያደርገው ፈለገ፡፡ በቀጣዩም ማለዳ ፣ መሬቱ እጅግ ረጥቦ ቆዳው ግን ደረቅ ነበረ፡፡



ጌዲዮን ሰላሳ ሁለት ሺህ ሰራዊት ይዞ ነበረ የወጣው፡፡ እግዚአብሔር ወደ ሶስት መቶ ሰዎች ብቻ አሳነሰው፡፡ እግዚአብሔር “የገዛ ክንዴ አዳነችኝ” እንዳይል ፈልጓልና፡፡ እግዚአብሔር ብቻውን የእስራኤል አዳኝ ነበረና፡፡



ጌዲዮን አሁንም ድረስ እንደፈራ በማወቅ ፣ አንድ ምድያማዊ ለሌላኛው የነገረውን ሕልም በሚስጥር እንዲሰማ እግዚአብሔር ፈቀደለት፡፡ ሕልሙም ፣ ትንሽዬ ዳቦ ወደ ምድያማዊያን ድንኳን እየተንከባለለች ስትመጣና ስታፈርሰው ነበረ፡፡



ሌላኛው ጥበቃ እጅግ ፈርቶ ነበረ፤ “ይሔ የጌዲዮን ሰይፍ ነው....” አለቀሰ፡፡ ጌዲዮን ሕልሙን ሲሰማና ትርጉሙን ሲያውቅ ፣ እግዚአብሔር ድልን እየሰጠው እንዳለ አስተዋለ፡፡



ጌዴዎን በምሽት የሚያካሂደውን ጥቃት አቀደ። እያንዳንዱን ወታደር ጡሩምባ ሰጠ ፤ በውስጡ መብራት ያለውን ባዶ ማሰሮም ሰጣቸው። እነርሱም ፤ ምድያማዊያን ሰራዊቶችን ከበቡ።



በጌዲዮን ምልክት ፣ ወታደሮቹ ጡሩምባቸውን ነፉት ፣
እንስራቸውን ሰበሩት እናም ውስጡ ያለውን ችቦ ለኮሱት፡፡
እንዴት ያለ ረብሻ ነው! እንዴት ያለ ግራ መጋባት ነው!
እጅግ ፈርተው የነበሩ ምድያማዊያንም ተነሱና ሮጡ፡፡



ከዚህ ታላቅ ድል በኋላ ፤ የእስራኤል ሰዎች ይመራቸው ዘንድ ጌዲዮንን ጠየቁት፡፡ ጌዲዮንም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው " በእናንተ ላይ መሪ አልሆንም ፤ እግዚአብሔር ይምራችሁ"፡፡ የሰዎችን ህይወት የመግዛት መብት ያለው እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ አውቆ ነበረ፡፡



የጌዲዮን ታናሹ ሰራዊት

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

መሳፍንት 6-8

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን
እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል።
የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን
አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት
እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው።
ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ!
ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል
ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤
እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት
ለመሞት ሰትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ
ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን
ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና
እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16